
# ክራውን፤ አዴ ቱ ዘ ፍረሽ ከት
# (Crown: Ode to the Fresh Cut)




## የአር አይ ኤፍ (RIF) መምሪያ ለቤተሰቦች

**ጭብጦች (Themes)፤** ማህበረሰብ (Community)፤ ባህል (Culture)፤ በራስ መተማመን (Self-confidence)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** ፅጉር መስተካከያ ቤት ወንድ ልጆች የሸከላ ቋጥኝ መስለው ገብተው፤ የንጉሳዊነት፤ በራስ መተማመን እና ዓለምን ለማሸነፍ ዝግጁ የመሆን ስሜት ይዘው የሚወጡበት የለውጥ ቦታ ነው። አዲስ ጸጉር መቆረጥ መልካቸውን ከማስተካከሉም በላይ ገደብ የለሽ እምቅ ችሎታቸውን ያስታውሳቸዋል።

**ደራሲ፡**
ደሪክ ባርነስ
(Derrick Barnes)

**ሰዓሊ (Illustrator)፤**
ጎርዶን ሲ. ጄምስ
(Gordon C. James)

## የንባብ ጊዜ!



**በፊት፤** የታሪኩን ርዕስ ያንብቡና ሽፋኑን ይመልከቱ። ልጅዎ በታሪኩ ውስጥ ምን ይሆናል ብለው እንደሚያስቡ ይጠይቁት።

**በንባብ ጊዜ፤** በሚያነቡበት ወቅት፤ “ልጁ ምን ዓይነት የጸጉር ቁርጥ ነው የጠየቀው?” በማለት ይጠይቁ።

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ፤**

- የጸጉር አሰራሩ ልጁ ምን እንዲሰማው አደረገ?
- ልጁ ስለ ጸጉር አስተካካዩ ምን ይሰማዋል? ምንድነው እንደዚህ እንዲያስቡ ያደረገዎት?
- ልጁ ቀጥሎ ምን ያደርጋል ብለው ያስባሉ?

## ሆን ተብሎ የሚደረግ ንግግር (INTENTIONAL TALK)

**ከጽሁፉ ባሻገር ማሰብ (Thinking Beyond the Text)**ለአዳዲስ አንባቢዎች ማዳበር የሚገባቸው ጠቃሚ ክህሎት በሚያነቡት እና በዙሪያቸው ባለው ዓለም መካከል ግንኙነት መፍጠር ነው። በዚህ መንገድ የራሳቸውን ሃሳብ ወደሚያነቡት ነገር አምጥተው ስለ አንድ ታሪክ ወይም ጽሑፍ የበለጠ ግንዛቤን ያዳብራሉ። እንዲሁም ሃሳባቸውን እና አመለካከታቸውውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይረዳቸዋል። ክራውን፤ አዴ ቱ ዘ ፍረሽ ከትን *(Crown: Ode to the Fresh Cut)* በሚያነቡበት ወቅት ልጅዎ የራሳችሁን ማህበረሰብ የሚያስታውሳቸውን የታሪኩን ክፍል ወይም ይህን መጽሃፍ ከማንበብ በፊት ያዩዋቸውን ነገሮች እንዲያገኝ ያበረታቱት።

## ተዛማጅ ተግባራት

**የማህበረሰብ የጸጉር መስተካከያ ቤት/ሳሎን**
(Community Barbershop/Salon)

በሚቀጥለው ጊዜ በአካባቢዎ የሚገኘውን የፀጉር አስተካካይ ቤት ወይም ሳሎን ሲጎበኙ በመጽሐፉ እና በፀጉር ቤት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ያስተውሉ እንደሆነ ይመልከቱ።
ንግግሮችን ያዳምጡ እና ሰዎቹን ያስተውሉ.
ሰዎች በመጀመሪያ ወንበር ላይ ሲቀመጡ እና ሲጨርሱ ምን ይሰማቸዋል?



## ተጨማሪ ሪሶርሶች (ADDITIONAL RESOURCES)



**ደሪክ ባርነስ (DERRICK BARNES) የተጻፉ ሌሎች መጻህፍት**

- ዘ ኪንግ ኦፍ ኪንደርጋርተን (The King of Kindergarten (2019))
- አይ አም ኤቭሪ ጉድ ቲንግ (I am Every Good Thing (2020))
- ካይንድ ኦፍ ዘ ክላስሮኦም (Kind of the Classroom (2020))

©2025 Reading Is Fundamental

Reading Is Fundamental | Read for Success Early Childhood